# "ቅንጅት ኢንተርናሽናል አመራር"(KIL)
# የእውነተኛ ማንነታቸው መጋለጥና የመጨረሻው ክስረት

ኃ/ልዑል ግርማ
ከዋሽንተን ዲሲ

በውጭ አገር ተፋፍሞና ተቀጣጥሎ የነበረው ጸረ ወያኔ ትግል በአንድ ጊዜ እንዴት ሊዳፈንና ሊቀዘቅዝ ቻለ? ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ተብሏል። ብዙ ምክንያቶችም ቀርበው ሰምተናል። በአጭሩ ባለፈው ዓመት ባለ 52 ገጽ በውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊ ትግል ማፈኛና ማዳከሚያ ሰነድ ከወያኔ ቢሮ አፈትልኮ ሲወጣ ብዙዎቻችን አንብበን ስናበቃ "ነፃነት ባለበት አገር ስለምንኖር ማንም ጫፋችንን አይነካንም" ብለን በየዋህነት ተዘናጋን። እየሰማን የማናዳምጥ እያየን የማንመለከት ሆነና ነገሩ የደከምንበትንና ብዙ መስዋዕት የከፈልንበትን ትግል አይናችን እያየ ልናስነጥቅ ነበር። ደግነቱ ቢዘገይም አሁን አከተመ። ወያኔ የአግአዚ ጦር ወይም ወታደር ወደ እኛ መላክ እኮ አያስፈልገውም። ቀላሉና አቋራጭ መንገድ እኛኑ መከፋፈልና ማዳከም ስለሆነ የውስጥ ሰዎችን በመካከላችን መላክ ነበር። ለመከፋፈልና ለማዳከም ደግሞ አስቀድሞ የታቀዱት ግለሰቦች ጥሩ ጊዜና አመቺ ቦታ አግኝተው የውስጥ ስራቸውን ከጀመሩ ሰነባበቱ። ዛሬ ይህንን አውቀን የተላኩብንን የውስጥ መሰሪዎች ለይተን ማግለልና በማያወላውልና በጠራ አቋም በፊት የቆምንለትን ዓላማ በተጠናከረና በጋራ ይዘን እንሰለፍ እንጨኽ እንታገል ነው የዚህ ጽሑፍ መልዕክት።

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌና አቶ ብርሃነ መዋ እንዴትና መቼ ከትግሉ አናት ላይ ተፈናጠው እንደወጡ ልብ ሳይባል በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉበትን ትግል ከንቱ አድርገው፣ ጀግኖች መሪዎቻችንን መስዋዕት የሆኑበትን ትግል ቀምተው፣በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞችን ትግል ዋጋ ቢስ አድርገው፣ በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ የተደገፈውን ትግል ተስፋ ሰርቀው፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ትግል ወደ ኋላ ጎትተውና ከፋፍለው እነርሱ በፈለጉት መንገድ ሲያስኬዱት እያየን ግራ የገባው ተመልካች መሆናችን በራሱ ግራ የሚያጋባ ነው። አብዛኞቻችን የመጡበትን ተልዕኮ ምን እንደሆን አለማወቃችንም ይሆናል። ትልቁና ዋናው ዓላማቸው ትግሉን መቆጣጠር፣ ተቃዋሚውን ማዳከምና መከፋፈል ነበር። በድብቅ የተዶለተው ሴራ ደግሞ ከወያኔ ጋር ተደራድሮ ሥልጣን የሚጋራ ኃይል በውጭ ጠላቶቻችንና በወያኔ አማካኝነት ቅድመ ዝግጅት ጨርሰው በተግባር ለመተርጎም በሂደት ላይ ነበሩ። ልቡና ፍላጎቱ አገር ቤት ያለውን ትግል ማገዝ የሆነው የውጭ ነዋሪ በኑሮ ውጥረትና ሩጫ ለዝርዝር ነገሮች ጊዜ ሳይሰጥና ሳይመረምር እነዚህ አደገኛ ሰዎች ትግሉን እንዲመሩ መጠበቁ ከየዋህነት አልፎ ትልቅ ስህተት ነበር። በቃሊቲ መሪዎች ስም በመጠቀማቸው ሀሰትነቱን ያላወቀውና የተወናበደው ተከተላቸው። የተቃወመው ሳይቀበላቸው ቀረ። ግራ የገባው ደግሞ ከሁለቱም አልሆንም ብሎ እቤቱ ተቀመጠ። የሚፈልጉት ትግሉን ማዳከም ነውና ከትግሉ ገሸሽ ያለው ግራ የተጋባው ለእነርሱ እንደ ትልቅ ሥራና እንደ ድል ይቆጥሩታል። እነርሱ ቅድመ ዝግጅት አድርገው የሚናገሩትን እያዳመቁ የሚያወጡ የሚዲያ ክፍሎችን ይዘው የሀሰት ዜና በማናፈሳቸው ሕዝቡን ግራ ማጋባትና ማወናበዱ ቀላል ሆኖላቸዋል።

እስቲ ከራሳቸው የሀሰትና የማወናበድ ስራዎች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት።

1. አሁን በስልክ ቃሊቲ ተገናኝተን ነበር ከሚለው የውሸት ቃል ጀምሮ፣ ለወሰኑት ጉዳይ በ24 ሰዓት ድጋፍ ሲመጣ ከቃሊቲ፣ ጽሑፍ ተፃፈ ከቃሊቲ ይባልልናል። መጨረሻም ቃለመጠይቀም ከቃሊቲ ሲባል ለመስማት

ጆሮአችንን ጣል ካደረግን ከረምን:: ለመስማት የጓጓንለት ቃለመጠይቅ የውሃ ሽታ ሆነ:: ታስታውሱ እንደሆን በአቶ አንዳርጋቸውና ብርሃነ ቅንጅት ኢንተርናሽናል ድኅረ ገጽ በጀንዋሪ መጀመሪያ ላይ አቶ ሙሉነህ እዩኤል የቅንጅት ዋና ጸሐፊ ቃለ መጠይቅ እንዳደረጉ፣ በቃለመጠይቁም እንደተጠቀሰው አቶ ሙሉነህ "የኤርትራ ሬዲዮ ጣቢያ ጭምር እንደሚያዳምጡና እንዲያውም አረብኛ ቀንቂ እየለመዱና እያሻሻሉ መሆኑን፣ የአቶ መለሰን አብዮታዊ ዲሞክራሲን ለማንበብ ጊዜ እንዳገኙ፣ የ ዴቪድ ሄልድስን የዲሞክራሲ ሞዴልን መጽሐፍ እያነበቡ" መሆናቸውን ይገልጽና ዝርዝር ዜናውን እናቀርባለን ካሉ 180 ቀናቶች አለፉ:: የት ገባ ቃለ መጠይቁ? ዛሬ ይህ ጥያቄ ሲነሳ ብዙ ምክንያቶች ሊያቀርቡ ይሞክራሉ:: መጀመሪያውኑ ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽም ባላፈርሽ ነው የተባለው: አዎን ጥያቄው አይቀርም ማነው ቃለመጠይቅ ያደረገላቸው? መቼ? እንዴትስ? ምን ምንስ አሉ? የሚለው ሊመጣ ነው ለዚያ የሚሰጡት መልስ ደግሞ እንደ " ከቅንጅት መሪ ለአዲስ ዓመት የተሰጠ መልዕክት" ብለው እንደሞከሩት የሀሰት ዜና የሚያስበላቸው ስለሆነ ይመስላል የውሃ ሽታ ሆኖ የቀረው:: ለአቶ ሙሉነህ ደህንነት አስበን ነው ካሉ ደግሞ መጀመሪያውኑ ዜናውን ባላወጡት ለማንኛውም በቃላቸው አለመቆማቸውን አሳይተው አልፈዋል:: ከታች በተጠቀሰው አድራሻ ራሳቸው ያወጡትን ማየት ትችላላሁ:: የተናገሩት ከሚጠፉ ...... ነው ያሉት አበው ሲተርቱ::

http://kinijitethiopia.com/docs/news/mulunehnews.htm

2. ሌላው በማዕከላዊ እስር ቤት እስረኞች ሲገረፉ ብለው ፎቶግራፍ ደርድረው በነብርሃነና አንዳርጋቸው (kinijitethiopia.org) ድኅረ ገጽ ላይ አወጡ:: ነገሩ ፈጽሞ ሀሰት መሆኑ ድብደባውና ስቃዩ በሌላ አገር ማለትም በኢስት ቲሞር ውስጥ የተፈፀመ መሆኑን በማስረጃ ሲወጣ፤ ስዕሎቹን አነሱ:: አንዳንድ ድኅረ ገጾች የተሳሳተና ያልተረጋገጠ ማስረጃ በማቅረባቸው ሕዝቡን በይፋ ይቅርታ ሲጠይቁ የነአቶ አንዳርጋቸው ወይም የቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ ድኅረ ገጽ ይቅርታም አልጠየቀ ለእነርሱ ሀሰት ተናግሮ ዓይንን በጨው ማጠብ የለመዱት ነገር ነውና::

3. ይባስ ብሎ ከጥቂት ወራቶች በፊት በሀገር ቤት ከየካቲት 5 ቀን 1999 ጀምሮ "ሰላማዊ የሕዝብ አመጽ" በኢትዮጵያ እንዲካሄድ ትእዛዝ አወጡ:: ተማሪው ትምህርት ቤት እንዳይሄድ፣ ሰራተኛው እንዲለግም፣ ሕዝቡ ከሥራ ውጭ በየመንገዱ እንዳይዘዋወር እቤቱ እንዲቀመጥ፣ ታክሲና ከባድ መኪና የሚያሽከረክር በዝግታ ስራውን እንዲሰራ ወዘተ... ብለው ትእዛዝ ሰጡ:: ምን ማለታቸው ነው? የኢትዮጵያ ሕዝብ የእነ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ትእዛዝ ተቀብሎ ወያኔን ያወርድልናል ነው ወይስ ተማሪውን ለማስጨረስ የታቀደ ተንኮል? ስንት ኢትዮጵያዊ ነው የኢንተርኔት ተጠቃሚ የሆነውና እድሉ ያለው? ቢኖረውስ ቃሊቲ የታሰሩት መሪዎቹ የሚሰጡትና ከብርሃነና ከአንዳርጋቸው ጽጌ የሚሰጠውን ትእዛዝ ለይቶ አያውቅም ነውን? አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሸሽተውና ጥለውት የሄዱትን ሕዝብ ነው ከስንት ሺህ ማይልስ ርቀት አምጽ የሚሉት? ባለፈው ዓመት የነአንዳርጋቸው ግንባር ቀደሙ ተዋናይና የኢትዮያን ሪቪው ድኅረ ገጽ ባለቤት አቶ ኤልያስ ክፍሌ ብቻ የሚያውቀው "የተግባር ሊግ" የተባለውን የሀሳብ ድርጅት ሕዝባዊ አመጽ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲነሳ እቤቱ ኮምፒውተሩ ፊት ለፊት ሆኖ በኢንተርኔት አስተላልፎ ነበር:: ያንን ዛሬም እነ አቶ አንዳርጋቸውና ብርሃነ መዋ ተቀብለው ደገሙት:: እንደሚባለውማ ከሆነ ሰሞኑን ሀቀኛ የቅንጅት ደጋፊዎችንና አባላት እየተጠቆሙ ይያዛሉ :: ነገሩ እንዴት ነው? ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት አቶ ኤልያስ ክፍሌ የኢትዮጵያ ሪቪው ድኅረ ገጽና የቅንጅት ኢንተርናሽናልን መመስረት ቀዳሚ ዜና አቅራቢ፤ አዲስ አበባ ውስጥ ያልተያዙ የቅንጅት አመራር መኖርያ ቤት ደውሎ "እርዳታ ገንዘብ ልንልክ ነውና አገናኙኝ" ብሎ ቤተሰባቸውን በስልክ እየደወለ ያሉበትን

ሲያውቅ በስልካቸው አማካኝነት ሶስት የተደበቁ ሰዎች በወያኔ ደህንነት መያዛቸውን አንዘነጋውም:: ዛሬም የዚያን ዓይነት ስራ እየተሰራ ነው:: ጊዜ ደግሞ ሁሉንም ነገር ያወጣዋል::

4. ሌላው ልንገነዘበው የሚያስፈልገው እውጭ ባለው ኢትዮጵያዊ ማለትም በትግሉ ዙሪያ ልምድ ያላቸው ሰዎች ላይ ከትግሉ ገለል እንዲሉ ዘመቻ እየተካሄደ ነው እግረ መንገዱን እነብርሃነ ያሰለጠኗቸውን ካድሬዎችና የተወናበዱ አንዳንድ ተከታዮቻቸውን በመተካት እነርሱ በፈለጉት መንገድ ሊቆጣጠሩ መሞከራቸው ነው:: በውጭ ያለው ነዋሪ በዘር፣ በፆታ፣ በዕድሜ ወይም በአካላዊ ቅርጽ አድልዎ እንዳይደረግ ሕጋቸው ይከለክላል:: ያንን ሲያደርግ የተገኘ በሕግ ይቀጣል:: ይህንን ሕግና አሰራር በተለመደበት አገር እየኖርን በእድሜ ገፋ ያሉት እንዲያውም ከሃምሳ ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ያሉትን ከትግሉና ካመራር መወገድ ወይም መገለል አለባቸው ወጣቱ ብቻ ነው መምራት መታገል ያለበት የሚሉት ፈሊጥ አምጥተዋል:: ይህንን በየፓልቶኩ በየሬዲዮው ቃለመጠቅ የነብርሃነ መዋ ሰዎች በይፋ ይናገራሉ:: እጅግ ያሳፍራል:: አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እና አቶ ብርሃነ መዋ እድሜያቸውን በሁለት አሥርታት ወደ ታች ሸመጠጡት ወይስ አብዮት ኢትዮጵያ ውስጥ ሲካሄድ ጡጦ የሚጠቡ ሕጻናት ነበሩ? ምንድነው ዓላማቸው? ዜግነትና የዜግነት ግዴታን መወጣት ወይም ለሀገር መቆርቆርና መታገል በእድሜ ሆነ እንዴ? ወይስ የታቀደ ደባ አለ? ወጣቱ ክፍል ይግባ ይስራ ማለት አንድ ነገር ነው አለበለዚያ 50፣ 60 እና 70 ዓመቱ የሆነ ኢትዮጵያዊ አርፎ ይቀመጥ ምንም አያገባውም ለማለት ማነው መብት የሰጣቸው? የተከበሩና ብዙ የሥራም ሆነ የሕይወት ልምድ ያካበቱና አንቱ የሚባሉት እኮ ናቸው ቃሊቲ እየማቀቁ የሚገኙት፣ ለስደት የተዳረጉት፣ በጥይት ግንባራቸውን የተመቱት ታዲያ በእነርሱ ላይ እኮ ነው ዘመቻ እያካሄዱ ያሉት:: የቅንጅት መርህ እኮ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያካተተ እንጂ ከ35 ዓመት እድሜ በታች ላሉት የሚል ሀረግ የለውም:: አጅሬ ልደቱም ይችን አባባል ይደጋግማት ነበር:: የሱን ፈለግ ተከታይ አግኝቷል::

5. በየከተማው ሁለትና ሶስት ካድሬዎች እየመለመሉ በእነርሱ አማካኝነት የድጋፍ ድርጅት መስርተናል እያሉ በተመሳሳይ ስም ሕዝቡን ግራ የሚያጋቡትን ለይቶ ማወቅና ማሳፈር ያስፈልጋል:: ሀሰተኛውን ከእውነተኛው ለይቶ ለማወቅ ተመሳሳይ ስም ያለው ለጊዜው ግራ ሊያጋባ ይችል ይሆናል:: የሚያብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ እንዳልሆነ አሁንም ተመሳሳይ ስም እየተጠቀሙ ቅንጅት ነን የቅንጅት ድጋፍ ነን እያሉ ቢያወናብዱም እውነቱን ለይቶ ማወቁ ደግሞ አስተዋይነት ነው:: ማንን እንመን ማንን እንከተል? ይላሉ አንዳንዶቹ ጠይቆ ማወቅ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሃላፊነት ሲሆን፤ እነአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ዋና ዓላማቸው ሕዝቡን ግራ ማጋባት፣ መበተንና ተስፋ ማስቆረጥ ነው:: ተመልከቱ በሁለት ቀን ማስታወቂያ በሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሰልፍ በሚወጡበት የዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ሕዝቡ ምን ያህል ግራ እንደተጋባና ሰልፍ የሚወጣው ሕዝብ ቁጥር እጅግ በጣም እንደቀነሰ:: ባለፈው ዓመት በክረምት ሻማ ይዞ በዝናብ በበረዶ ለሊት ከቀን ውሎ አድሮ አልነበረም ሕዝቡ ሲታገል የነበረው? እድሜ ለእነ አቶ ብርሃነ መዋ:: እድሜ በየፓልቶኩ ሕዝቡን ለሚያደነቁሩ ካድሬዎቻቸው ዛሬ ያ ሁሉ የለም:: ባለፈው ፌብርዋሪ 2007 ዓለምን የተቆጣጠሩ ያህል ስራ ብዙ ሆነው 24 ሰዓት የሰሩበት "ዓለም አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ" አንዱ ከተማ 11 ሌላው ከተማ 17 አንዳንድ ከተማ ከ20 እስከ 25 የሚደርሱ ተከታዮቻቸው ሲሆኑ የታዩት ትንሽ ቁጥሩ ወደ መቶ የተጠጋው በሁለት ከተሞች ብቻ ነው:: ለምን ወጡ አይደለም ነጥቡ :: ሰልፍ አደረግን ለማለት ብቻ ሕዝቡን ከፋፍለው ለውጭው እና ለራሳችንም በሚያሳፍር ቁጥር መውጣቱ ነው:: ለማስረጃም ያህል በአትላንታ ከተማ የወጡት 15 የማይሞሉ ሰዎች በአካባቢው ቴሌቭዥን ጣቢያ ተነስቶ የታየውን እንደጀብዱ ያወሩት ይሆናል በድኅረ ገፃቸውም ይታያል:: የመከፋፈል



EthioLion.com

ትርፉ ይህ ነው:: እነ አቶ አንዳርጋቸውና ብርሃነ ቅንጅትን ከፍለው ድርሻቸውን ይዘው ለመሄድ ያደረጉት ሙከራ ውጤቱን አይተውታል:: ይማሩ ይሆን ? ፈጽሞ:: ቢሳሳቱ ኖሮ አዎን ይባል ነበር ግን የፈለጉትን ነው ያደረጉት:: እስከ ዛሬ የታገሰው ታገሰ ግራ የተጋባው እጁን አጣምሮ ተቀመጠ:: ከአሁን ወዲያ በዚሁ መቀጠል የለበትም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ እነአቶ አንዳርጋቸው ጽጌንና ብርሃነ መዋን የሚያውቃቸው በጸረ ወያኔነት ሳይሆን ለወያኔ ያገለገሉ ያደሩ በመሆናቸው ነው:: ታዲያ በውጭ ያለው እንዴት ይህንን ማወቅ ተሳነው?

6. ሲጀምሩ ትግሉ ተዳከመ፣ ትንሽ ቆይቶ ገንዘብ ባከነ፣ ከዚያም ገንዘብ ተዘረፈ እያለ ድጋፉን ይሰጥ የነበረውን ሕዝብ መንፈስ ለማሳዘንና ከትግሉ እንዲሸሽ በመሞከር ከፍተኛ አፍራሽ ቅስቀሳ በማካሄድ፣ በውጭ ያለውን ሕዝብ ድጋፉንና እምነቱ ለመሸርሸር የተቀነባበረ ዘመቻ በየፓልቶኩና በሬዲዮም ሆነ በኢንተርኔት ያሰራጨው ይኸው አጥፊ ቡድን ነው:: ሀያ አራት ሰዓት ፓልቶክ ክፍል ከፍተው የወሬ አሉባልታ ሲያናፍሱ የሚውሉና የሚያድሩ እሳት የላሱ ካድሬዎችን ነው እነ አቶ አንዳርጋቸው ያስቀመጡልን:: አሁን ማንነታቸው ታውቆ እየተጋለጡና ሕዝብ እየራቃቸው ነው::

"የቅንጅት መሪዎች ታቦት እኮ አይደሉም እኛም ትግሉን መምራት እንችላለን" ብለው መሪዎቻችን በታሰሩ ሳምንት ሳይሞላ ነው ሕዝብ የመረጣቸውን መሪዎች ሥልጣን የቂመ

ጡለት:: በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ስብሰባ ላይ "ቅንጅት እኔን ፈልጎ መጣ እንጂ እኔ ቅንጅትን ፈልጌ አልመጣሁም" ካሉት ከአቶ አንዳርጋቸው ምን ይጠበቃል? አቶ አንዳርጋቸው፤ በሬ ወለደ ባይኔ አይቻለሁ እመኑኝ ቢሉም መደነቅ አያስፈልግም:: በሬ ወለደ ብለን ከማውራታችን በፊት ግን እናስብ:: እውነቱን እንመርምር:: የፖለቲካ አክሮባት መስራት ለአቶ አንዳርጋቸው አዲስ ነገር አይደለም ነው:: ድሮስ ከአቶ መለስ ዜናዊ ጓደኛ ምን ይጠበቃል? የወያኔን ትልቁን ሥራ በዘር መከፋፋልና ማደራጀትን በተግባር ያሳዩትና የቀሰቀሱት አቶ አንዳርጋቸው ናቸው እኮ:: የአማራው ሕዝብ ከየት ወዴት የሚለውን መጽሀፋቸውን ያነበበ ሰው አቶ አንዳርጋቸው ምን ዓይነት መርዘኛ ሰው መሆናቸውን ያሳያል:: የኢትዮጵያን ታሪክ በመቶ ዓመት የወሰኑትና የወያኔን ዓላማ ያስተጋቡ ሰው ናቸው:: አገር ሲገነጠል፣ ሕዝብ በዘሩና በቂንቂው ሲገደል፣ እነ ፕሮፌሰር አሥራት ሲታሰሩ፣ የአዲስ አበባ ሕዝብ ፍዳውን ሲያይና በላስቲክ ቤት ውስጥ በክረምት ሲሰቃይ እሳቸው በወያኔ የማዘጋጃ ቤቱ ባለሥልጣን ነበሩ:: ትላንት የቅንጅት ምርጫ ሊካሄድ ሶስት ሳምንት ሲቀረው አዲስ አበባ ገቡና ቆዳቸውን ለመቀየር ሞከሩ:: ነጻነት የማያውቅ ነጻ አውጪ የሚለውን መጽሐፋቸውን እንደተራማጅና እንደ ጸረ ወያኔ ያስቆጥረኛል ብለው ከተመጻደቁ መጽሐፉ ከስሙ በቀር በብዛት የሚያወራው ስለ ፊውዳል ሥርዓት ስለ አማራው ጨቂኝነት ወዘተ ነው:: ድሮስ ወደ ሜዳ ገብተው ሌሎች የትግል ጓደኞቻቸውን ከድተው ከነመለስ ጋር ወያኔ ጎራ አንድ ዓመት ሲቀመጡ ለዕድሜ ልክ የሚበቃ የወያኔነት ክትባት መከተባቸውን ያረጋገጡልን ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ ሮጠው የተቀላቀሉ ጊዜ ነው:: ለንደን ኢንግላንድ ሳሉም ታማኝነታቸውና ጓደኝነታቸው ለአቶ መለስ መሆኑ እርሳቸው ዘንድ የሚያርፉት ምን ያህል ታማኝና ወዳጅ መሆናቸውን ያስረዳል:: ዛሬ በአንድ አፍ ሁለት ምላስ ባይሆኑብን ምን አለ:: ባለፈውም ዓመት ከለንደን ሆነው አዲስ አበባ የሰሩት ድራማም ወቅቱን ጠብቆ ወደፊት ለሕዝብ ይፋ ይሆናል:: የወያኔ ደህንነት ክፍል ካሌንድር የያዙ ሕጻናትን ሲገድል ለአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የተኛበት ጉዳይ አልገባ ብሎናል:: ቃሊቲ እስር ቤት ለእርሳቸው ብቻ የፈለጉትን ለማድረግና በቁጥጥራቸው ሥር ስለመሆኑ የተናገሩትን አይዘነጉትም መቼም:: የአገርቤቱም "ከቃሊቲ ጋር ያደረጉት" የቴሌኮንፈረንሱም ታሪክ ይወጣል :: ከምርጫው በፊት የነበሩትን 11 ዓመታት ምን ሲሰሩ ነበር? አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አይታመኑም:: መርሳት የሌለባቸው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ አያምናቸውም:: ይህ ማለት ደግሞ አቶ ብርሃነ መዋ ይታመናሉ ማለት አይደለም:

በሀገር ቤት ቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ ሕዝቡን ከዳር ዳር አደራጅቶ ጨርሷል ይሉናል። እንዴት መቼና ማን አደራጀው? የአቶ አንዳርጋቸውና ብርሃነ የፓልቶክ ካድሬዎች ይሆኑ እየዞሩ ያደራጁት? አቶ አንዳርጋቸውና ብርሃነ በድብቅ አገር ቤት ገብተው ነው ያደራጁት እኮ እንዴት? በላፕቶፓቸው እየዞሩ ነው ያደራጁት? አዎን ሁለትና ሶስት ካድሬዎች እውጭ አገር በየከተማው እየተከሉ የዚህ ከተማ ድጋፍ የዚያ ከተማ ድጋፍ ይሉናል። አንዱን ዌብ ሳይት 7 ጊዜ በተለያየ ከተማ ስም በመፍጠር ሥራ የተሰራ ለማስመሰል ይሞክራሉ። "ጽድቁ ቀርቶ በውን በኮነነኝ" አሉ አገር ቤት አደራጅተን ጨርሰናል ማለቱን ትተው በራሱ ፈቃድ በራሱ ጊዜና ገንዘብ የተሰባሰበውን የውጭ አገር ድጋፍ ድርጅት መከፋፈልና ማፈራረስ ቢተው ምን ያህል ትግሉን በደገፉ ነበር።

7. እስቲ ደግሞ እነ አቶ ብርሃነ መዋ ከተናገሩት ውስጥ፤ ኖቬምበር 12 እና 13/2006 በአትላንታ ከተማ ተገናኝተው አንድ ሚሊዮን ዶላር በስድስት ወር ለመሰብሰብ ቃል ተገባ ተወሰነ ብለው ጠዋትና ማታ ሲያደነቁሩን ነበር። ስብሰባው 8ኛ ወር ሆነው ስድስት ወርማ ካለፈው ሰነበተ። ምንም አልሰማንም። አሁን ባለፈው ሰሞን 24 ሺ ዶላር እንደደረሱ ነው የሰማነው ምን ነካው? አሁንም በሀሰት የፈረደባቸውን ሻለቃ ስም ሊያነሱ የሀሰት ፕሮፓጋንዳም ሊነዙ ይሆን? አይሉም አያደርጉም አይባልም። ያቺ 24 ሺማ ለሁለቱ የ3 ወር ደሞዝም አትበቃም። ለማንኛውም እነ አቶ አንዳርጋቸው ማን እንደሆኑና ምን እየሰሩ መሆናቸውን ያልተረዳ ሙልጭልጭና ተለዋዋጭ ቃላቸውን ማስተዋልና ስራቸውን ማየት ብቻ በቂ ነው። ትልቅ ጥፋት የጠፋው ገና ከመጀመሪያው እርምጃ አለመወሰዱ ነበር። አዎን በሬ ሰርቆ ይሰቀል ሲባል እናቱ ማልቀስዋን ሲያይ አዩ እማዬ ዛሬ ምን አስለቀሰሽ በእንቁላሉ ጊዜ በቀጣሽኝ ኖሮ እዚህ ደረጃ አልደርስም ያለው ታሪክ ብጤ ሆነ ነገሩ ሁሉ።

8. ባለፈው ሰሞን ደግሞ እነ አቶ ብርሃነ መዋ በፓልቶክ ክፍላቸው የምርጫ 97 ውጤት ተረስቶ፣ የሕዝብ ድምጽ ጥያቄ ተሰርዞ፣ የሞቱት ወገኖቻችን ደምና አጥንት ከንቱ ሆኖ፣ የተገረፉት የቆሰሉት የተሰደዱት ጉዳይ ተዘንግቶ ይባስ ተብሎም የታሰሩት መሪዎቻችንና የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንደሌሉ ተቆጥሮ፤ ለምርጫ 2010 እንዘጋጅ ማለታቸው ድብቅ ዓላማቸው ምን እንደሆነ ያመላክታል። እርሱም ከቃሊቲ የመጣ ትእዛዝ ነው ይሉን ይሆን? አይሉም አይባልም። የዚህ ለሚቀጥለው ምርጫ እንዘጋጅ ጉዳይ፤ ወገኖች፤ ምስጢሩም ይሁን ትርጉሙ ይግባችሁ። አላልንም እናስተባብላለን ካላችሁ በፓልቶክ ሲደሰኩሩ የተቀዳው ማስረጃ አለ። አይክዱት ነገር።። አቶ ብርሃነ መዋ ወያኔ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር የወር ደሞዛቸው 475 የኢትዮጵያ ብር የማያልፈው እድሜ ለወያኔ ሚሊየነር ለመሆንና የንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ለመሆን የበቁት ለወያኔ በታማኝነታቸው ነው። ከአቶ መለስ ጋር በየአውሮፕላን ጣቢያው ከኋላ ኋላ እያቶሶቶሱ እጆቸውን ወደ ኋላ አጣምረው ሲከተሉ እድሜ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ብዙ ጊዜ ታይተዋል። ሚሊየነር የሆኑበት የንግድ ተቋማቸው እስካሁን በሰላም እየሰራ መሆኑ ሚስጥሩና ምክንያቱ ምን ይሆን? ሌላው ነገር ይሄስ ባካባቢ ልጅነት "እኔን የማይፈልጉኝ አኮ የዚህ አካባቢ ሰዎች ናቸው ምክንያቱም እኔ የዚህ አካባቢ ሰው ስለሆንኩ" እያሉ የጠባብነት መርዝ በመርጨት ያካካቢዎን ሰዎች መቀስቀስ የሚያቆሙትስ መቼ ነው? ቅንጅት ባካባቢ ልጅነት ነው እንዴ የተደራጀው? ተከታዮቻቸውስ ምን ያህል አርቆ የማሰብ ችሎታ እንዳላቸው በእውነቱ ያሳስባል። የወያኔን ፈለግ መከተላቸው ልብ ሊባል ይገባል።

EthioLion

9. ቅንጅት፤ የሰላም፣የፍቅር፣ የመቻቻል፣ የመወያየት መንፈስ ነው እያሉ ሊቀመንበር ነኝ የሚሉት ዶክተር ሞገስ ገብረማርያም ደግሞ ሁሌም የሚያወሩት በተቃራኒው ነው። ለመሆኑ ዶክተር ሞገስ ገብረማርያም ትላንት ምን ሲሰሩ እንደነበር የሚዘነጋ ይመስላቸዋል ይሆን? ዶክተርነቱን ያገኙት ድርጅት በመከፋፈልና በመበተን ሙያ ይመስላል። የቀድሞው መድሕን ፓርቲ አባላት ያውቁታልና ይናገሩት። ዶክተር ሞገስ ገብረማርያም ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ከጥቂት ዓመት በፊት የሄዱ ጊዜ ምን ምን እንደሰሩ፣ ከማን እንደተገናኙና ምንስ ለመስራት እቅድ ይዘው እንደመጡ የማይታወቅ ይመስላቸው ይሆናል። ከወያኔው ፕሬዜዳንት ከመቶ አለቃ ግርማ ወልደጊዮርጊስ ጋር ለመገናኘት ቤተመንግሥት መግባታቸውን ልካድ ቢሉም አይክዱት ነገር ነው። ለመሆኑ አትላንታ ካሉት ወዳጃቸው ጋር በ5ሺህ የሚቆጠር ካሬ ሜትር የከተማ ቦታ እንዴት ሊያገኙ ቻሉ? ከፖሊስ ኮሚሽነሩ ሐሰን ሺፋ ጋር መገባበዙና ወዳጅነቱስ ምን የተደበቀ ምሥጢር ይኖረው ይሆን? እሱንም ለመካድ እንዳይሚይሞክሩ ተስፋ አለኝ። እንዲያው ወዳጅነታቸውን በማስመስከር የቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ ሊቀመንበር ነኝ በሚሉት ከተማ እንኳን የወያኔን የፖሊስ ኮሚሽነር የዛሬ 3 ወር ገደማ አሜሪካ የመጡ ጊዜ ለሳምንት እቤታቸው አሳርፈው ጮማው ሲቆረጥ ውስኪው ሲንደቀደቅ አልነበረምን? በቤታቸው ያፈለጉትን የመጋበዝ መብት አላቸው ግን ከማን ጋር ነው ጥያቄው። ከሕዝብ ጠላት ጋር? ከወያኔ ባለሥልጣን ጋር? አዬ የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ተብዬዎች በዚያም በዚህም ከወያኔ ጉያ አልወጣ አላችሁ። በሬዲዮ ሄዶ መለፍለፉ ኃጢያታችሁን ቢያፀዳው ጥሩ ነበር ግን እየጨመራችሁበት ነውና አያዋጣም።

10. የተለየ አመለካከት ወይም ተቃውሞ ያለው ሰው ለመናገር ይቅርና ምነው ሰዎች እባካችሁ እንደዚህ ዓይነት አጸያፊ ቃልና አሳፋሪ ባሕል ተው ያላችሁ እንደሆን የሚወርድባችሁ የስድብና መረን የለቀቀ ንግግርና ዛቻ አያድርስ ነው። በቅርቡ አቶ ዳዊት ከበደ ማንም ሳይጠይቃቸው እራሳቸውን በማጋለጣቸው ሳናመሰግናቸው አናልፍም። አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ ይላሉ እንዲህ ነው። ነጋም ጠባም ለሊትም ቀንም ከሰዓት በኋላም ያንኑ ተመሳሳይ የስድብ መዓት ሲያወርዱ ይውላሉ። በዚህ በዚህ የካልጋሪ፤ ካናዳ ብዙ ወንድማገኝን ወይም ሙያዬን የሚስተካከል የለም። ሰሞኑን ከመሳደብዋ ብዛት የአዕምሮ መነካት ሳይደርስባት እንዳልቀረ ይገመታል። ከፓልቶኩም አልፈው በየከተማው እነርሱን ያልደገፈ ይወገዛል ስሙ ይጠፋል። ለመሆኑ መደገፍ በፈቃድ ነው እንጂ በግዴታ፣ በዛቻ፣ በማስፈራራት፣ በመሳደብ እኮ አይደለም። ያ የተሸናፊዎች መንገድና የደካሞች ጎዳና ነው። መናገር መለፍለፍ ሌላ መስራት ጥረት ማድረግ ሌላ ነገር ። የወያኔ 52 ገጽ መመሪያ በትክክል እኮ ነው በሥራ ላይ የዋለው።

11. የዚያን ሰሞኑ ሰላምና የእርቅ የሚሉት ፈሊጥ አምጥተው የዌብሳይትና የድርጅት መሰል የግለሰቦች ስብስብን በመዘርዘር ከወያኔ ጋር እንደራደር የሚሉት ነገር ጨርሶ ከንቱና የማወናበድ ተግባር ነው። አንድ ዌብሳይት አንድ ባለቤት ወይም ሁለትና ሶስት ሰዎች ሊያካሂዱት ይችላሉ። ታዲያ እነዚህ ግለሰቦች የትኛውን የህብረተሰብ ክፍል ነው ወክለው የሚደራደሩት። የምን ራስን ማታለል ነው? በምን ዓይነት መንገድ ነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መደራደር የሚችሉት? ከፈለጉ እኮ ቲኬታቸውን ቆርጠው አገር ቤት መግባት መብታቸው ነው። የምን ሕዝብን ግራ ማጋባት የምን ማወናበድ ነው የያዙት።

በአጭሩ መሪዎቻችን ይፈቱ፣ የሕዝብ ድምጽ ይከበር የሚለውን ወቅታዊ የትግል ጩኸት ሊያዘናጉና ትግሉን ሊያዳፍኑ ወይም ተቆጣጥረው ወያኔ በፈለገው መንገድ ሊመሩት ነውና ከአሁን ወዲያ ግራ መጋባት ይቁም። ከግንቦት 14 ቀን 2006 ጀምሮ ብዙ ጊዜና የሰው ኃይል ባክኗል። አገራችን እጅግ ውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ እየገባች ነው ያለችው። ስለዚህ ተዘጋጅተን እንደቀድሞው በቆራጥነትና በአንድነት እንታገል። ለነብርሃኑ፣ አንዳርጋቸውና ዶክተር ሞገስ ብለን ወይም ጥቂት ግለሰቦች ብለን ዋና መስዋዕትነት የከፈሉትን መሪዎችን

EthioLion.com

Ethiopia Will Prevail!

አንዘንጋ። አገር ወዳድ ወገን ሁሉ እንደቀድሞው ተሰባሰብ፣ እርዳ፣ ድምፅህን አሰማ። ሌላ መንገድና አማራጭ የለህም። ብርሃነ መዋ እና አንዳርጋቸው ጽጌ የቅንጅት መሪዎች አይደሉም። ሊሆኑም አይችሉም ተከታዮቻቸውም እጣ ክፍላቸው ያው ነው። አክትሞላቸዋል። ይህን የጥፋት ጎዳና እንዲያርሙ የመጨረሻው ዕድልም ቢሰጣቸው አልተጠቀሙበትም። ዛሬ ከጨዋታው ውጭ ሆነዋል። ከትግሉ ሩሕ ውጭ ወጥተዋል። እኛ ግን በማስተዋልና በቆራጥነት ለመታገል ብርታቱን ይስጠን። ጠንካራ፣ ኢትዮጵያዊ ብቃት ያለው አመራር ሲኖር አብሮ ከመስራት ውጭ ስም ማጥፋቱ የዚያን ግለሰብ ወይም ድርጅት አቂምን ነው የሚያጋልጠው።

ቆራጥ፣ በትግል የተፈተኑ፣ በወያኔ እስር ቤት የተሰቃዩት ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት ይህን ከፍተኛ ኃላፊነት ሲወስዱ በደስታና በጋለ መንፈስ መቀበል ነበር እንጂ ማውገዝ፣ መሳደብና ስም ማጥፋት ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ሲወገር ድንጋይ እንዳቀበለው ዓይነት ሥራ መስራታችሁ ነገ ድንጋዩ በእናንተው ላይ እንደሚወርድ አትጠራጠሩ። የቅንጅቱን ፕሬዚዳንትንም በለመደ አፋችሁ ለማሳደብ እንደማትሞክሩ ተስፋ አደርጋለሁ። ለማንኛውም አልቆላችኋል። ሰመጣችሁ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ኃይለ ልዑል ግርማ

EthioLion.Com